ፍትሐ ነገሥት ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ መነኰሳትና የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ መምህር)

ጳጕሜን ፪፣ ፳፻፲፯ ዓ.ም

ፍትሐ ነገሥት ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

፩. ፍት.ነገ.1፥10 ምእመን ያልሆኑ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ መከልከል ይገባል ማለት ነው? ምእመን ያልሆኑ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ ይችላሉ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ አሥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ የሚገባቸው ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው። ከዚያ ውጭ የተወገዘ ሰውና እምነቱ ሌላ የሆነ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም። አንዳንድ ጊዜ የሌላ እምነት ሰዎች ለቀብርና ለሌላም ጉዳዮች ተከትለው ሊመጡ ይችላሉ። አክብረን በግልጽ ብንነግራቸው እነርሱም ደስ ብሏቸው ከውጭ ይጠብቁናል። እንዲህ ነው መሆን ያለበት።

፪. ፍት.ነገ.1፥9 ላይ "ኤጲስ ቆጶሱ በቤቱ ይቀድስ" ይላል። ሁሉንም የቅዳሴውን ሥርዓት በቤቱ ያከናውን ማለት ነው? ኤጲስ ቆጶስ ቤት ውስጥ ታቦት አይታጣምና ይላል ታቦት ከመቅደስ ውጪ ሌላ ቦታ ይቀመጣል ማለት ነው?

መልስ፦ በኤጲስ ቆጶስ ቤት ወይም ከቤቱ አጠገብ ታቦት ይኖራል። ሲጀምር የጳጳስ ቤት ከቤተክርስቲያን አጠገብ ይሆናል። ለቡራኬ፣ አዲስ ለሚተከል ቤተክርስቲያን የሚሆኑ ታቦታትም በቤቱ ይኖራሉ። ስለዚህ በችግር ጊዜ ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ባይችሉና ወደ ጳጳሱ ቤት ግን መሄድ የሚያስችል ሁኔታ ቢፈጠር ወደ ጳጳሱ ሄደው ቀድሶ ሊያቆርባቸው ይችላል። በሰላም ዘመንና ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ በሚያስችል ሁኔታ ላይ ግን ከጳጳስ ቤት ሥርዓተ ቅዳሴ ሊፈጸም አይገባም።

፫. ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ማን ነው?

መልስ፦ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን አይሁዳዊ ሲሆን እስከ 70 ዓ.ም አካባቢ ድረስ የነበረውን የእስራኤልን ታሪክ የጻፈ ሰው ነው። ይህ መጽሐፉም እንደ ሦስተኛ መቃብያን ተቆጥሮ ከ81ዱ አሥራው መጻሕፍት ይቆጠራል። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን በሐዲስ ኪዳን ዘመን የነበረ ሰው ቢሆንም የጻፈው መጽሐፍ ከብሉይ ጀምሮ የሚናገር በመሆኑ ሊቃውንት ከብሉይ ኪዳን ቀኖና መድበውታል።

፬. ፍት.ነገ.1፥5 በመሠዊያው የዮሐንስ ወንጌል ያንብቡ ይላል። መቼ ነው የሚነበበው?

መልስ፦ አዲስ ቤተክርስቲያን በተሠራ ጊዜና ቅዳሴ ቤቱ ሲከናወን በመሠዊያው (በታቦቱ) ላይ ተደርጎ የዮሐንስ ወንጌል ይነበባል። ይኸውም ዮሐንስ በጌታ አጠገብ ይቀመጥ ስለነበር የዚህ ምሳሌ ነው። ታቦቱ የጌታ፣ ወንጌለ ዮሐንስ የዮሐንስ ምሳሌ ነው።

፭. ፍት.ነገ.3፥32 ሳይጠመቅ ዓመት የሞላው ወይም ያለፈው ሕፃን መቼ ነው የሚጠመቀው?

መልስ፦ ቢቻል ዓመት ሳይሞላው ወንድ ከሆነ በአርባ ቀኑ፣ ሴት ከሆነች በሰማንያ ቀኗ ይጠመቁ። በዚህን ቀን ካልተቻለ ግን ከዚያ በኋላ ባለው በማናቸውም ቀኖና በማይከለክለው ቀን መጠመቅ ይችላል። ዙሮ ዙሮ ማዘግየት አይገባም።

፮. የቅብዐ ቅዱስና የሜሮን ልዩነት ምንድን ነው?

መልስ፦ ቅብዐ ቅዱስ መጀመሪያ የሚቀባው ቅባት ነው። ቅብዐ ሜሮን በኋላ የሚቀባ ቅባት ነው። ቅብዐ ሜሮን ለጥምቀት፣ ለክህነት ጳጳሳቱ ወይም ቀሳውስቱ የሚጠቀሙት ነው። ቅብዐ ቅዱስ ግን ስንታመም የምንቀባውና በማናቸውም ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ነው።

፯. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3 ላይ ንኡስ ክርስቲያን ከመጠመቃቸው በፊት ኃሙስ ገላቸውን ይታጠቡ፣ አርብ ይብሉ፣ ቅዳሜ ይጹሙና እሑድ ይጠመቁ ይላል። ቅዳሜ መጾም ይቻላል?

መልስ፦ ይህ የተነገረው በትንሣኤ ለሚጠመቁ ሰዎች ነው። ከትንሣኤ በፊት ያለችዋ ቅዳሜ (ቀዳም ሥዑር) ትጾማለች። በሌሎች ቅዳሜዎች ለብዙ ሰዓት እየቆዩ መጾም ግን አይቻልም።

፰. በዕድሜ ትልቅ ሴት ስትጠመቅ ካህን ከአንገቷ በላይ ሜሮን ይቀባል። ሌላውን ሴት ዲያቆናዊት የካህኑን እጅ ይዛ ትቀባ ይላል። ዲያቆናዊት ሴት ምንድን ናት?

መልስ፦ ዲያቆናዊት ሴት የምትባለው ስልሳና ከዚያ በላይ ዓመት የሆናት ሴት ሆና፣ በአንድ ባል ጸንታ ኖራ ባሏ የሞተባት፣ ሴቶችን እንድታስተባብር በጳጳሱ በአንብሮተ እድ ሳይሆን በቃል የምትሾም ሴት ናት።

፱. ኤጲስ ቆጶስ እና ቄስ ያጥምቁ ዲያቆን አያጥምቅ ይላል። አንዳንድ ጊዜ ቤት ውስጥ የታመመ ሰው ቢኖር እና ቄስ መጥቶ ጸበል መርጨትና ማጥመቅ ባይችል ዲያቆን ማጥመቅ (መርጨት) ይችላል?

መልስ፦ ኤጲስ ቆጶስና ቄስ ያጥምቁ ዲያቆን ደግሞ አያጥምቅ የተባለ የልጅነት ጥምቀት ነው። ጸበል መርጨት ግን ዲያቆንም ይችላል።

፲. አምላካውያት መጽሐፍት ሲቆጠሩ እንዴት ነው? ለምሳሌ መጽሐፈ ባሮክን ዝርዝር ውስጥ አላየሁትም? ስምንቱ የሥርዓት መጽሐፍ ልክ እንደወንጌላት የምንቀበላቸው ናቸው ወይ? ማለቴ ወንጌል አይሻሻልም እነዚህ ግን ሊሻሻሉ የሚችሉ ከመሆናቸው አንጻር ሚዛናቸው እንዴት ነው?

መልስ፦ መጽሐፈ ባሮክ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር ተደርቦ ይቆጠራል። ተረፈ ኤርምያስ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ ተረፈ ባሮክ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር ተደርበው ይቆጠራሉ። ኩፋሌ ከኦሪት ዘፍጥረት ጋር ተደርቦ ይቆጠራል። ስምንቱ የሥርዓት መጻሕፍት አዎ እንደ

ወንጌል ነው የምንቀበላቸው። ሥርዓት ሊሻሻል እንደሚችል መነገሩ ክብሩን አይቀንሰውም። ጳውሎስ ያገባ ጳጳስ ይሁን አለ። ሠለስቱ ምእት ደግሞ ያላገባ ቢሆን ብለው ሠሩ። እንዲህ ስለሆነ የጳውሎስ መልእክት ክብሩ ቀነሰ ማለት አይደለም። የማይሻሻለው ዶግማ ነው። ዶግማ ደግሞ በወንጌልም፣ በመልእክታትም፣ በሥርዓት መጻሕፍትም ይገኛል። ቀኖና ግን ሊሻሻል ይችላል። ቀኖና ደግሞ በወንጌልም፣ በመልእክታትም፣ በሥርዓት መጻሕፍትም ይገኛል።

፲፩. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሁለት ላይ ሥጋዉን ደሙን ያልተቀበሉ ምእምናን ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ በር ይጠብቁ ይላል። እነማን ናቸው የሚጠብቁ?

መልስ፦ የሚጠብቁ በር ጠባቂዎች (ዐፀውተ ኀዋኀው) የሚባሉ ከአሥሩ መዓርጋተ ክህነት አንደኞቹ ናቸው። አሁን በተግባር እየተተገበረ አይደለም።

፲፪. አንድ ንዑሰ ክርስቲያን ከተጠመቀ በኋላ ለምሳሌ ቀድሞ ድንግል ባይሆን ከተጠመቀ በኋላ ካህን መሆን ይችላል?

መልስ፦ አይችልም። ኢአማኒ ሆኖ ኖሮ ቢጠመቅና ቀድሞ በሌላ እምነት ሳለም ድንግል ሆኖ ሲጠመቅም በዚሁ ንጽሕና ከቀጠለ እስከ ጵጵስና መድረስ ይችላል። አግብቶ ወይም ድንግልናውን አፍርሶ ኖሮ ቢጠመቅ ግን በምእመንነቱ ይቀጥላል እንጂ አይካንም አይጸጽስም።

፲፫. የሊቀ ጳጳሳት፣ የጳጳስ እና የኤጲስ ቆጶስ ልዩነት ቢያብራሩልኝ?

መልስ፦ ኤጲስ ቆጶሳት የሚባሉት አዲስ ተሿሚዎች በየሀገረ ስብከቱ የሚሾሙ አሁን "የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ" እየተባሉ የሚጠሩት ናቸው። አሁን ግን ስሙ ጠፍቶ ሲሾሙ ብቻ ኤጲስ ቆጶሳት ይባላሉ እንጂ ከተሾሙ በኋላ ቀጥታ ሊቀ ጳጳስ እየተባሉ ነው የሚጠሩት። በቀድሞው ዘመን ጳጳስ የሚባለው የተወሰኑ ሀገረ ስብከቶችን ኤጲስ ቆጶሳት በበላይነት የሚመራ ነው። በሌላ አገላለጽ መጥሮጶሊስ ይባላል። ሊቀ ጳጳሳት የሚባለው ደግሞ የኤጲስ ቆጶሳቱም የጳጳሳቱም የበላይ አሁን ፓትርያርክ የሚባለው ነው። ሊቀ ጳጳስ የሚለው ስያሜ ግን ሰዋስዋዊ አቀራረቡም ልክ አይደለም። ጳጳስ ቢል ይቀናል። ሊቀ ጳጳስ ከተነገረም ለፓትርያርኩ ነው። ለእያንዳንዱ ጳጳስ የበላይ ናቸውና። ከዚያ ውጭ ላለው መነገሩ ግን ልማድ ይመስላል።

፲፬. ፍት.ነገ.4፥47 የጵጵስና መናብርት (sees) ይበላለጣሉን?

መልስ፦ ከእግዚአብሔር በሚያሰጡት ጸጋ ከሆነ አይበላለጡም። ሁሉም እኩል ናቸው። በአቀማመጥ፣ በፍርድ፣ በአፈ ጉባኤነት ግን በስምምነት ቅዱሳን ሊቃውንት አፈ ጉባኤነትን ለእስክንድርያ፣ ፍርድን ለሮማ፣ ቡራኬን ለኤፌሶን፣ ቅዳሴን ለአንጾኪያ ሰጥተው ሥርዓት ሠርተዋል።

ጥ፮. ፍት.ነገ.4፥41 መንበረ ቶማስ፣ መንበረ ተክለ ሃይማኖት የሚባል የለም ማለት ነው? ያሉት አራት መንበራት (apostolic sees) ብቻ ናቸውን?

መልስ፦ በሐዋርያት ዘመንና በኒቅያ ጉባኤ በዓለም ላይ አራት መናብርት ብቻ እንዲኖሩ ሥርዓት ተሠርቶ ነበር። ነገር ግን የመንፈሳዊ ሹመት ዓላማው ወንጌል በዓለም በየቋንቋው እንዲዳረስ በመሆኑ፣ ሥርዓት ደግሞ በየወቅቱ መለዋወጥ የሚችል ስለሆነ አሁን በየሀገሩ ፓትርያርክ እንዲሆን ሆኗል። መንበረ ቶማስ የሕንድ፣ መንበረ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ የዕጨጌነት መንበር ነው። የኢትዮጵያ በሐዋርያዊነት መንበረ ማርቆስ ነው። ይህ ስያሜ መሰጠቱ ቅዱሳኑ ለሀገሪቱ ባበረከቱት አበርክቶ ነው።

ጥ፯. ፍት.ነገ.አን 4፥40 አራቱ ሥርዓታተ ዓለም፣ አራቱ ነፋሳት፣ አራቱ የፍጥረት ጠባይዕ እነማን ናቸው?

መልስ፦ አራቱ ሥርዓታተ ዓለም የሚባሉት አራቱ ወቅቶች ናቸው። እነዚህም ክረምት (Summer)፣ መጸው/ጥቢ (Spring)፣ ሐጋይ/በጋ (Winter)፣ ጸደይ/ተወን (Autumn) ናቸው። አራቱ ነፋሳት የሚባሉት በተፈጥሮ ያሉ አራት ነፋሳተ ምሕረት ስምንት ነፋሳተ መዓት አሉና ከእነዚህ የምሕረቶቹ አራቱ ናቸው። አራቱ የፍጥረት ጠባይዕ የሚባሉት አራቱ ባሕርያት በመባል የሚታወቁት እሳት፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ መሬት ናቸው።

ጥ፰. ፍት.ነገ.፩፥፩፬፩ ላይ "በአንዲት አገር ውስጥ ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ሊሾሙ አይገባም" ይላል። አገር ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ ከዚህ በአንዲት አገር ማለቱ በአንዲት ሀገረ ስብከት ማለቱ ነው።

ጥ፱. በሰንበት ቀን ንግድ መነገድ አይቻልም ይላል። ቅዳሜን ይጨምራል ወይስ እንዴት ነው?

መልስ፦ እንደ ፍትሐ ነገሥት በሰንበት ቀን ቅዳሜም እሑድም፣ በጌታ በዓላትና በእመቤታችን በዓላት ገበያ እንዳይኖር ያዝዛል። ይህ ደግሞ አሁን ላይ እንደ ልምድ ከተቀበልነው ጋር ይራራቃል። የሆነው ሆኖ ግን ፍትሐ ነገሥት አዎ ከልክሏል።

ጥ፲. አንድ ካህን በማይገባ ነገር ወይንም በግል በሆነ ጉዳይ ከእሱ በታች ያሉትን ዲያቆናት ወይም ምዕመናን ቢያወግዝ ውግዘቱ ይሠራል ወይስ እንዴት ይታያል? ውግዘቱ የማይሠራ ከሆነስ የተወገዙት ሰዎች ምን ማድረግ አለባቸው? ዝም ማለት ነው ወይስ ከኤጲስቆጶሱ ሐዲው መፈታት አለባቸው?

መልስ፦ ከካህናት ወገን ጥፋት የሌለበትን ሰው በከንቱ ያወገዘ ካለ ራሱ የተወገዘ ይሆናል ተብሏል። እንደዚህ ዓይነት የገጠመው ሰው ካለ ለሚመለከተው የበላይ አካል ነግሮ ጳጳሱ በሚለው መልኩ ይኑር። አንዳንድ ጊዜ ሳናውቀው አጥፍተንም ስለሚችል ጳጳሱን አናግረን ያለንን ማድረግ ነው።

፳፫. እኔ በአደኩበት አህጉረ ሰብክት ከአህጉረ ስብከታቸው ውጭ ጎረቤት አህጉረ ስብከት ሐዲው ክህነት የሚቀበሉ አሉ ይሄስ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ከሀገረ ስብከታቸው ውጭ ፈተና ፈርተው ወይም በሌላ ምክንያት ከሌላ ሀገረ ስብከት ክህነት መቀበል አይገባም። ባለማወቅ ተደርጎ ከነበረም ለወደፊት ይህ እንዳይሆን ማስተማር ነው።

፳፬. ፍት.ነገ.5፥103 የሐራ ጥቃ ጥምቀት ሲል ምን ማለት ነው? ሐራ ጥቃ ምንድን ነው?

መልስ፦ ሐራ ጥቃ የሚባሉት ቃል ሥጋ ኮነ ያለውን መነሻ አድርገው "ተለወጠ" ያሉ ከሓዲያን ናቸው።

፳፭. ፍት.ነገ.5፥108 ላይ "ሥጋ ግን ለዘለዓለም አይብላ" ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ለዘለዓለም የሚለው ለብዙ ጊዜ፣ ደረቱ ይሙላ ፊቱ ይቅላ ብሎ አስቦ አይብላ ለማለት ነው። እንጂ ሥጋ መብላት ርኩስ አለመሆኑን ለማሳወቅ በትንሣኤ፣ በልደትና በመሳሰሉ በዓላት ቢበላ ኃጢአት አይሆንበትም። (በሐዋርያት ሲኖዶስ ተገልጿል)።

፳፮. ፍት.ነገ 4፥61 ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት ሊፈታ ይችላል?

መልስ፦ አዎ ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት በማናቸውም ጊዜ መፍታት ይችላል።

፳፯. ከዚህ በፊት በነበረው ኮርስ የኤጲስ ቆጶስ ምግቡ የጣመ የላመ ይሁን ይል ነበረ። በፍትሐ ነገሥት ደግሞ የላመ የጣመ አይቅመስ ይላል አይቃረንም?

መልስ፦ አይቃረንም። ያን ጊዜ የጣመ ይብላ መባሉ ስለ ክብረ ጵጵስናው ነው። ከዚህ አይብላ መባሉ ደረቱ ይሙላ ፊቱ ይቅላ ብሎ የላመ የጣመ አይቅመስ ተብሏል። የላመ የጣመ ይብላ የተባለ ለሰውነቱ እንዲመቸው አይደለም። ስለክብረ ጵጵስናው ነው እንጂ።

፳፰. የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎቻቸው ወገን በራሳቸው ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሾሙ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ ሥርዋጽ እንደሆነ በአባቶቻችን ተነግሮናል። ሥርዋጽ ማለት ሌሎች ሰዎች ያስገቡት ግላዊ ሐሳብ ማለት ነው። ስለዚህ ሥርዋጽ ደግሞ ቋሚ ፈራጅ ስላልሆነ አንቀበለውም ማለት ነው።

፳፱. አንዲት ሴት ብቻ ካለችበት ቤት ያደረ ኤጲስ ቆጶስ የክርስቲያን ሃይማኖት እንዳይነቀፍ ከሹመቱ ይሻር። ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ኤጲስ ቆጶስ እንግዳ ሆኖ እንኳ ቢሆን ማደር ያለበት ከሄደበት ሀገር ቤተክርስቲያን ፈልጎ ከዚያ ነው። ከሄደበት ሀገር ቤተክርስቲያን ከሌለ በደግነታቸው

የተመሰከረላቸው ወንዶችም ካሉበት ቤት ያድራል። ይህ ሁሉ በዝሙት እንዳይጠረጠርና ምእመናንን እንዳያሰናክል ነው።

፷፯. ፍት.ነገ.6፥212 አምስት ሰዎች የልመሰከሩለት አንዱ ስንኳን ቄስ አይሁን ሲል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?

መልስ፦ ቄስ ከመሾሙ በፊት በሿሚው ጳጳስ ፊት ስለመልካምነቱና ይህ ክህነት እንደሚገባው የሚመሰክሩ ቢያንስ አምስት ሰዎች መኖር አለባቸው ማለት ነው።

፷፰. ፍት.ነገ.6፥211 ቄስ ከሠላሳ ዓመት በታች ከሆነ አይሾምም ማለት ነው?

መልስ፦ አዎ አይሾምም። በሥርዓት ደረጃ በተለየ መገለጥ ወይም ትእዛዝ ካልሆነ በቀር ቅስና የሚሾም ሰው ሠላሳ ዓመት ሳይሆነው መሾም የለበትም።

፷፱. ፍት.ነገ.7፥249 ዲያቆን ማስተማር አይችልምን?

መልስ፦ ይችላል። አሕዛብን ካስተማሩ በኋላ ማጥመቅ ስላለ አስተምሮ ማጥመቅ እንደማይችል ለመግለጽ የተነገረ ነው። እንጂ ትምህርትን ብቻ ማስተማር ይችላል። ለዚህ ማስረጃችን ደግሞ ሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ ነው።

፸. ፍት.ነገ.8፥267 ንፍ*ቅ ዲያቆናት የእግዚአብሔርን ንዋየ ቅዳሳት መንካት አይገባቸውም ይላል። በቅዳሴ ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስ ማሳለም፣ አትሮንስ ማቀበል፣ ጥላ መያዝ እና ጸበል ማደል አይችሉምን?

መልስ፦ ንዋየ ቅድሳት የተባሉትን ነገሮች ሁሉ መንካት የሚችለው ዲያቆንና ከዚያ በላይ ክህነት ያለው ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱሱ፣ አትሮንሱ፣ ጥላው ንዋየ ቅድሳት ተብለው ከተቀደሱ (ለቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት ከተለዩ) በኋላ ምእመን ሊነካቸው አይገባም።

፸፩. ፍት.ነገ.6፥222 ላይ መዋት (ውሽባ ቤት) ምንድን ነው?

መልስ፦ ውሽባ ቤት የሚለው ማሳጅ ያለበት ሻወር ቤት ነው። ስለዚህ ከእንደዚህ ዓይነት ቤት ምእመናን ሊገቡ አይገባቸውም ማለት ነው። በተለየ ታመው ለመዳን አስፈላጊ ካልሆነ በቀር።

፸፪. ፍት.ነገ.7፥242 ዲያቆን 25 ዓመት ሳይሆነው አስቀድሞ አይሾም ይላል። ግልጽ አልሆነልኝም ቢያብራሩልኝ ማለትም አሁን ካለው አገልጋይ ዕድሜ አንጻር ጋር አያይዘው?

መልስ፦ ይህ ሥርዓት የተሠራው በመለካውያን ዘንድ ነው። በእኛ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ተምሮ ከተገኘ በዐሥር በዐሥራ ሁለትም መሾም ይችላል።

፴፫. ጌታን አገለግላለሁ እመነኩሳለሁ ብሎ ሚስቱን የፈታ ይሻር የሚለው አንቀጽ ቤቱን ሚስቱን ልጁን ስለኔ ብሎ ያልተወ ለእኔ ሊሆን አይገባውም ከሚለው ከወንጌል ቃል ጋር እንዴት ይታረቃል?

መልስ፦ በሃይማኖት ምክንያት ማለት እነርሱ የሌላ እምነት ተከታይ ሆነው እርሱ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ክርስትና ቢመጣ ለእርሱ መልካም ነው። ቤተሰቡን ትቶ ያልተከተለኝ ማለት የማያምኑ ቤተሰቦቹን ትቶ በእኔ ያላመነ ተብሎ ይተረጎማል። ይህ ለመነኰሳት ሲነገር አባት ከሆነ ለልጆቹ ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሳያደርግ፣ ልጅ ከሆነ እናት አባቱን ሳይረዳ እንዲሁ በችግር ትቶ መመንኰስ አይፈቀድም። አበምኔቱ ይህንን ሁሉ አረጋግጦ ነው ማመንኰስ ያለበት።

፴፬. አሁን ባለንበት አንድ ዲያቆን እስከ ስንት ዓመት ነው ሳያገባ በዲቁና የሚያገለግለው? ቅስናስ መቀበል የሚቻለው ከስንት ዓመት ጀምሮ ነው?

መልስ፦ እስካሁን ዲያቆን በዲቁናው እስከዚህ ዘመን ብቻ ያገልግል የሚል አላገኘሁም። ባለኝ መረዳት ዲያቆን ዲያቆን ሆኖ እስከ ዕለተ ሞቱም ሊቆይ ይችላል።

፴፭. ዲያቆን ድንግል ያልሆነችን ሴት (ዋሽታው) ቢያገባ ክህነቱ ይሻራል? ያገባትንስ ሴት መፍታት ይገባል?

መልስ፦ ዋሽታው ካገባችው በኋላ ድንግል አልነበርኩም ብላ ብትነግረውና ይህን ካወቀ በኋላ ከእርሷ ጋር ምንም ግንኙነት ካላደረገ ሌላ ሳያገባ በዲቁናው ሊቀጥል ይችላል። ከነገረችው በኋላ ከእርሷ ጋር ግንኙነት ካደረገ ግን ክህነቱ ይሻራል።

፴፮. ዲያቆናት ቀሳውስት በሌሉበት ጠበል መርጨት፣ የማዕድ ቡራኬ ቆርሶ መስጠት ይችላሉ?

መልስ፦ አዎ ይችላሉ።

፴፯. ቅብዐ ሜሮን ከማይደገሙ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አንዱ እንደሆነ ተምሬ ነበረ። እናም ቅብዐ ሜሮንን ለልጅነትም ለክህነትም ከተጠቀምንበት ክህነት የሚሰጠው ያው በሜሮን ልጅነቱን ያጸናው ሰው ስለሆነ ምሥጢሩን ደገመ አያሰኘውም? እንዴት ይታረቃሉ?

መልስ፦ ሜሮን ለጥምቀት አንድ ጊዜ እንቀባለን። እንደገና ሀብተ ክህነትን ለማግኘት ደግሞ ሜሮንን እንቀባለን። ሜሮን አይደገምም ያሉ ካሉ ከምን አንጻር እንዳሉ ራሳቸውን ጠይቋቸው። ምናልባት ለልጅነት አንድ ጊዜ ከተቀባን በኋላ ሁለተኛ ለልጅነት አንቀባም ለማለት ፈልገው ከሆነ ወይም ለክህነት አንድ ጊዜ ከተቀባን በኋላ ሁለተኛ ለክህነት መቀባት አይገባም ለማለት ፈልገው ከሆነ ልክ ናቸው። ሁለት ጊዜ መጠመቅና ሁለት ጊዜ ክህነት መሾም አይቻልምና።

፴፰. ብሉያትን ሐዲሳትን ያልተረጎመ ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያልተረጎመ ቅስና አይሾም ይላል። ይህን ካላወቀ አይሾምም ማለት ነው?

መልስ፦ አዎ ለመሾም ይህንን ማወቅ አለበት። አሁን አሁን ግን ከችግር የተነሣ ሊሆን ይችላል እየተተገበረ አይደለም። ነገር ግን መተግበር ያለበት መሠረታዊ የሠለስቱ ምእት ቀኖና ነው።

፴፱. አናጉንስጢስ ከብሉይ ኪዳን ከፍ ባለው ቦታ ቁሞ ሁለት ክፍል ያንብብ። አንዱ የዒዋዊ አንዱ የሚጠት ነገር ያለበትን ነው ይላል። ዒዋዊ እና ሚጠት ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ዒዋዊ ማለት ምርኮ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ወደ ባቢሎን እንደሚማረኩ ቅዱሳን ነቢያት ጽፈዋል ያ ይነበብ ማለት ነው። የምርኮው ዘመን አልቆ ደግሞ እንደገና እስራኤላውያን ወደ ሀገራቸው እንደሚመለሱ (ሚጠት) የጻፉ አሉ። ያንን ያንብቡ ማለት ነው።

፵. አንድ ሰው ግብረ ዲቁናን ተምሮ ነገር ግን በሕፃንነት ዕድሜው ባለማወቅ ከሴት የደረሰ ቢሆን ክህነቱ ይቀጥላል?

መልስ፦ አይቀጥልም። አፍርሷል።

፵፩. ዲያቆናዊት ሴት የምትሾመው ሴቶችን ለማገልገል ነው ይላል። ትልልቅ ሴቶች ሲጠመቁ ዲያቆናዊት ሴት መኖር አለባት። በአሁኑ ግዜ ዲያቆናዊት ሴት አለች? በዚሁ ዲያቆናዊት ሴት ብቻ ናት ሴቶችን የምታስተምር? ሴቶች ዲያቆናዊት ባይሆኑም ሴቶችን ማስተማር አይችሉም? ሴት ሆኖ ትልልቆችን ሳይሆን ሕፃናትን ወንድንም ሴትንም ማስተማር አይቻልም?

መልስ፦ ዲያቆናዊት ሴት መኖር እንዳለበት ፍትሐ ነገሥትም መጽሐፍ ቅዱስም ይነግረናል። በተግባር የሌለችበት ደብር ካለም እንድትኖር ማድረግ ነው። ሴቶችን በቤተክርስቲያን የምትቆጣጠር ዲያቆናዊት ሴት ናት። ከቤተክርስቲያን ውጭ ግን ማንኛዋም ሴት ሴቶችን ማስተማር ትችላለች። ከቤቷም ልጆቿን ማስተማር ትችላለች። በወንድ መካከል እንዳታስተምር ተከለከለች እንጂ በሴቶች መካከል አልተከለከለችም።

፵፪. ካህን ሚስቱ ከሞተችበት በኋላ ክህነቴን ጠብቄ እኖራለሁ ቢል በምንኩስና ነው መኖር ያለበት ወይስ እንዲሁ በቅስና እያገለገለ መኖር ይችላል እንደ በፊቱ ኑሮውን እያደረገ?

መልስ፦ መንኩስ ብሎ የሚያስገድደው ሕግ አላገኘሁም። ክህነቱን እንደያዘ ሌላ ሴት ሳያገባ እያገለገለ መቀጠል ይችላል። (በባህል ወይ አግባ ወይ መንኩስ ብለው የሚያስገድዱ አሉ)። መጽሐፍ ላይ ግን እስካሁን አላገኘሁትም።

፵፫. አንድ ምእመን ሳያገባ እንዲሁ እስኪሞት መኖር ይችላል? ሰው ማግባት አልያም መመንኮስ ነው ያለበት ይባላል። ይህ ትክክለኛ አስተምህሮ ነው?

መልስ፦ ወይ ያግባ ወይ ይመንኩስ የሚል መጽሐፍ ላይ አላገኘሁም። በእኔ አረዳድ ንጽሕናውን ጠብቆ እንዲሁ መኖርም ይችላል።

፶፬. ንፍ*ቀ ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖ መልበስ አይገባቸውም ይላል። ግን ቅዳሴ ላይ ይለብሳሉ አይጋጭም?

መልስ፦ አሁን ቅዳሴ ላይ ንፍ*ቀ ዲያቆን የሚሆነው ዲያቆኑ ራሱ ነው። በቀድሞው ዘመን ንፍ*ቀ ዲያቆን የሚባለው ግን መቅደስ የማይገባ ልብሰ ተክህኖን የማይለብስ ነው። አሁን ላይ በሹመት ደረጃ ንፍ*ቀ ዲያቆን የሚባል የለም።

፶፭. ሊቀ ዲያቆን የካህናት አለቃ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ ሊቀ ዲያቆን የካህናት አለቃ ነው ማለት ከእርሱ በታች ላሉ ካህናት ማለትም ለዲያቆናት፣ ለንፍ*ቀ ዲያቆናት፣ ለአናጉንስጢስ፣ ለዐፃዌ ሥጋት፣ ለመዘምራን አለቃ ነው ማለት ነው።

፶፮. ፍት.ነገ.9፥305 አንድ ሐኪም (ዶክተር) ክህነት ቢቀበል ዱክትርናውን የግድ መተው አለበት? አገልግሎቱን እስካላስታጎለ ድረስ ሁለቱንም ማከናወን አይችልም?

መልስ፦ ካህንም ዶክተርም መሆን ይችላል። ከዚህ ከፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ላይ እንደተገለጸው ከክርስቲያናዊ ሥራዎች አንዱ ሕክምና ነውና። ከዚህ ላይ የተነገረውም በዋናነት መንፈሳዊ ሥራውን የሚያስታጉል እንዳይሆን ነው። ሌላው ዋናው ግን ካህናት ሙሉ ሥራቸው ማስተማር፣ ማጥመቅ ሊሆን ስለሚገባ ተብሎ ከማንኛውም ዓለማዊ ሥራ እንዲለዩ ነበር። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን መተርጎም ያለበት ጉዳይ ነው።

፶፯. ፍት.ነገ.9፥278 አንድ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ስም (ስለ ሃይማኖቱ) ብሎ እስከ መታሰር መከራ ቢቀበል በደረሰበት መከራ ምክንያት ቅስና እንዳለው ከተቆጠረ ቀድሶ ማቁረብ እና ማጥመቅ (sacramental rites) መፈጸም ይችላል ማለት ነው?

መልስ፦ አዎ ይችላል። ነገር ግን ይህ ሰውየው ልዩ አምላካዊ መገለጥ ካገኘ ብቻ ነው። ለምሳሌ እንደ ዲያቆኑ ፊልጶስ ቅስና ማለት ነው። በሐዋርያት ሲኖዶስ በግልጽ እንዳየነው። ፊልጶስን ቅስና የሾሙት ሐዋርያት ሳይሆኑ ራሱ ጌታ ነው። ከዚያ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አጥምቋል።

፶፰. ፍት.ነገ.፮፥፪፻፶፬ ላይ "ሰውን ለመክሰስ ወደ ንጉሥ አይሂዱ" ሲል ምን ለማለት ነው? ፍትሕ የተጓደለበት ካህን ምን ማድረግ ነው ያለበት?

መልስ፦ ፍትሕ የተጓደለበት ካህን ወደ ኤጲስ ቆጶስ ሄዶ ማስፈረድ አለበት እንጂ ወደ ንጉሥ መሄድ አይገባውም።

፶፱. "ዲያቆናት ከመገዛት ነጻ ናቸውና በጸሎት ጊዜ ወገባቸውን በዝናር አይታጠቁ። ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ማንም አይገዛቸውምና" ይላል። ከመገዛት ነጻ ናቸው ሲል ከምን አንጻር ነው? ከመገዛት ነጻ ያልሆኑ እነማን ናቸው?

መልስ፦ ከመገዛት ነጻ ናቸው ማለት ከባርነት ነጻ ናቸው ማለት ነው። ዲያቆን የማንም ሰው ተገዢ መሆን የለበትም። ሌሎች ምእመናን ግን በችግር ወይም በሌላ ምክንያት በፈቃዳቸው ራሳቸውን ለሌሎች ሊያስገዙ ይችላሉ።

፷. ፍት.ነገ.፮፥፪፻፶፭ ላይ "በቁጣ ወይም ከዚህ ዓለም ሥራ በማናቸውም ሥራ ምክንያት አይከልክሉ" ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ካህኑ ተቆጥቷቸው ወይም ካህኑ በዓለማዊ ሥራ አልረዳችሁኝም ብሎ ሥጋውን ደሙን ከመቀበል ሊከለክላቸው አይገባም ማለት ነው።

፷፩. ፍት.ነገ 9፥286 አቡነ ቀሲስ (ኮሬ አቤስኮቤስ) ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ኮሬ ኤጲስ ቆጶስ የሚባለው ቆሞስ ነው። ይኸውም በመዓርግ ከኤጲስ ቆጶስ ዝቅ ያለ ከቄስ ከፍ ያለ ነው።

፷፪. ፍት.ነገ 9፥299 ላይ "ካህናት በሰርግ ሚዛዚቶቹ ሳይገቡ አስቀድመው ተነስተው ይሄዱ" ለምን እንዲህ ተባለ?

መልስ፦ ካህናት ዘፈን መስማት ፈጽሞ አይገባቸውም። ስለዚህ ዘፈን ሳይጀመር በልተው መርቀው ቀድመው መውጣት ይገባቸዋል ለማለት ነው። በካህናት ተናገረ እንጂ ሌላው ምእመንም ዘፈን ካለበት ቦታ መገኘት እንደሌለበት አንቀጽ 11 በእንተ ሕዝባውያን ላይ ተገልጿል። ፍሬ ሐሳቡ መጀመሪያውንም በሰርጉ ዘፈን አይኑር ማለት ነው።

፷፫. ፍት.ነገ 9፥342 የነባቤ መለኮት ጎርጎርዮስን የወርቅ እና የብረት ማኅተም ምሳሌን ቢያስረዱን።

መልስ፦ ከወርቅና ከብር በጽሩይነት ወርቅ የከበረ ነው። ነገር ግን አንድ የወርቅ ማኅተምና አንድ የብር ማኅተም ቢኖሩና በሁለቱም የንጉሥ ስም ቢኖርባቸው ማኅተሙ ወደ ወረቀት ሲታተም የወርቁና የብሩ ተመሳሳይ ይሆናል። በወርቅ የተመሰለ ደግ ቄስ እና በብር የተመሰለ በምግባር ዝቅ ያለ ቄስ ሁለቱም የሚያሰጡት ጸጋ እኩል ነው ማለት ነው።

፷፬. ፍት.ነገ 10፥353 ላይ "አገዳደሉ ያለ ፈቃዱ በእጁ ሆነ" ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አንድ ሰው ከድንገት ሰው ሊሞትበት ይችላል። ለምሳሌ ለአውሬ የተኮሰው ጥይት አልፎ ሰው ሊገድል ይችላል። ይህ አገዳደሉ ከልብ ፈልገው በፈቃድ ያላደረጉት

ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ገዳም ቢገባ መነኰሳት ይቀበሉት ሌላው ሊገድለው ቢመጣ እንኳ አሳልፈው አይስጡት ማለት ነው።

፻፷. ሆን ብሎ ሰው የገደለ ንስሐ ገብቶ መመንኰስ አይፈቀድለትም?

መልስ፦ ይፈቀድለታል።

፻፷፤. ፍት.ነገ.11፥423 ቀለም የተቀባ ጫማ መጫማት አይገባም ማለት ነው?

መልስ፦ በቀድሞው ዘመን ቀለም የተቀባ ጫማ እንዳይጫሙ ሥርዓት ተሠርቶ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ በዝሙት እንዳይወድቁና በትዕቢትና በከንቱ ውዳሴም እንዳይጠለፉ የሚል ነው። ከዚያ ውጭ ግን ምእመናን ይህንን ስሜት የማያመጣባቸው ከሆነ ያገኙትን የወደዱትን መልበስ እንደሚችሉ አንቀጽ 23 ላይ ተነግሯል።

፻፷፪. ለጣትህ የወርቅ ቀለበት አታድርግ ሚለው እና አሁን ሲጋቡ የሚያደርጉት ኃጢአት ነውን?

መልስ፦ ለጣት ቀለበት ማድረግ በተክሊል ጊዜ ቤተክርስቲያን የሚደረግ ነው። ይኸውም ከዚያው ከቤተክርስቲያን የሚቀመጥና ሥርዓቱ ካለቀ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ዕቃ ቤት ገብቶ የሚቀመጥ ነው። አሁን ግን ያገቡ ሰዎችም እያደረጉ ነው። ያገቡትን ካላገቡት ለመለየት ጥሩ ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ አላገኘሁትም። ሰሎሞን ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት ቀለበት ነበረው። ዙሮ ዙሮ ግን ምእመናን ቀለበት አያድርጉ ቀለበት ማድረግ የዝሙት ምልክት ነው ተብሎ ተገልጿል። ከዘመኑ ጋር ታይቶ በሲኖዶስ ቢተረጎም መልካም ነው።

፻፷፫. ሰው ሰርግ ቤት ሂዶ በእጁ አያጨብጭብ በእግሩ አያሸብሽብ ይላል። ዓለማዊ ሰርግ ላይ ነው ወይስ በቤተክርስቲያን በሚደረገውም ነው?

መልስ፦ ዓለማዊ ሰርግ የሚባል የለም። ማንኛውም ምእመን ቆርቦ ነው ማግባት ያለበት። ከማንኛውም ክርስቲያን ሰርግ ቤት ደግሞ ዘፈን ሊዘፈን አይገባም። በዝማሬ፣ በትምህርትና በሌሎችም መንፈሳዊ ተግባራት መከናወን አለበት እንጂ።

፻፷፬. ከሐራ ጥቃ ጋር አብሮ የቆረበ የቀደሰ ክህነቱ ይሻራል ይላል። በሀገራችን በአንዳንድ አካባቢ የቅባት እና ተዋሕዶ ካህናት እየታወቀም ይሁን ሳይታወቅ አብረዉ የሚቀድሱበት አጋጣሚ ይስተዋላል። ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ቅባት አስተምህሮው ስሕተት ነው። ነገረ ክርስቶስን የሚያፋልስ ትምህርት ነው። ስለዚህ ከቅባቶች ጋር አብሮ መቀደስ አይገባም። ማስረጃ ይዞ ለይቶ ከቤተክርስቲያን ማውጣት ይገባል። ከበላይ ያለ አካል ቸል ካለ ደግሞ የተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካለበት (እንደ ዲማ ጊዮርጊስ ካለ ቦታ) ሂዶ መጠመቅ ማስጠመቅ ይቻላል።

፷. የቁደር ጥምቀት መቼ መቼ ይፈጸማል?

መልስ፦ የቁደር ጥምቀት አንድ ሰው ትክክለኛዋን ሃይማኖት ክዶ ቢሄድና እንደገና ተጸጽቶ ወደ ትክክለኛዋ ሃይማኖት ቢመለስ ቁደር ይጠመቃል። ሁለተኛ አንድ ወንድ/ሴት ከሌላ ሃይማኖት ሴት/ወንድ ጋር ሩካቤ ቢያደርግ/ብታደርግ ቁደር ይጠመቃል/ትጠመቃለች። ሌላ ምክንያት ግን መጽሐፍ ላይ አላገኘሁም።

፷፩. ሐመደ ዕጎልት የተቀባ ካህን ቢሆን ይሻር ይላል። ሐመደ ዕጎልት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ሐመደ ዕጎልት በኦሪት ሕግ ይደረግ ከነበረ መሥዋዕት አቀራረብ የሚገኝ አመድ ነው። ካህን ወደ ኦሪት መሥዋዕት ተመልሶ ሐመደ ዕጎልትን ሊቀባ አይገባም። ከአይሁድ መሥዋዕትም ሊበላ አይገባም ማለት ነው።

፷፪. ጌታው ነጻ ያወጣው አገልጋይ ግን ክህነት ይሾም ይላል። ከዚህ ጌቶች የሚላቸው እነማንን ነው? ነጻ ወጥተዋል የሚለው ምን ዓይነት ነጻነት ነው?

መልስ፦ በቀድሞው ዘመን አንድ ሰው ሲቸገር በፈቃዱ ለሌላው ሰው ባሪያ (አገልጋይ) ሆኖ ይኖራል። በዚህ ጊዜ ተገዢው አገልጋይ ሲባል አገልጋይ የተሆነለት ሰው ደግሞ ጌታ ይባላል። አንድ ሰው ጌታው ፈቅዶለት ዲያቆን ከሆነ በኋላ ነጻ ሆኖ ይኖራል ማለት ነው።

፷፫. ራስ ቁር ያደረገ ካህን ቢኖር አራት ወር ከቤተ መቅደስ በውጭ ይቁም ይላል። ራስ ቁር ምንድን ነው?

መልስ፦ ራስ ቁር ከብረት ነክ ነገሮች ራስን ለመከላከል በቀድሞ ዘመን የነበሩ ወታደሮች ይለብሱት የነበረ የራስ ልብስ ነው። ካህን ወታደር መሆን አይችልም። እንደ ወታደር የራስ ቁር ማድረግም አይገባውም ማለት ነው።

፷፬. አንድ ቄስ ቅዳሴ ገብቶ ሳለ የታመመ ሰው መጥተህ አሰናብተኝ ብሎ ቢልክበት ቦታው ቅርብ ቢሆን ልብሰ ተክህኖውን እንደለበሰ ሐዲሙ ቃሉን ሰምቶ ይመለስ። ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ሐዲሙ ናዝዞ እግዚአብሔር ይፍታሕ ይበለው። ቦታው ሩቅ ቢሆን ግን ሰው ተክቶ ይሒድ። የሚተካ ቄስ ባይገኝሳ ቢሉ ሥጋው ደሙ የተሠራ ለሰው አይደለምን ቅዳሴው ይቅር ሄዶ ያሰናብተው። እንዴት ነው ይሄ በምን ዓይነት ሁኔታ ላለ ታማሚ ነው ሚፈቀደው? አሁን ለምሳሌ ልጅህ ሞተ ወይም ሚስትህ ሞተች ቢባል አቋርጦ ወይም ትቶ መሄድ ይቻላል ከተሰየመ በኋላ?

መልስ፦ ይህ ታምሞ እያጣጣረ ላለ ታማሚ የተነገረ ነው። ቄሱ የሚሄደውም ኃጢአት ሠርቶ ከነበረ ኃጢአቱን ሰምቶ ኑዛዜውን ተቀብሎት እንዲያርፍ ነው። ከሞተ ግን ቅዳሴ አቋርጦ መሄድ አይገባም።

፮፭. 12 ሆነው ይሾማሉና ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ በአንዲት ሀገር 13 ምእመናን ቢኖሩና ኤጲስ ቆጶስ ይሾምልን ቢሉ መሾም ይቻላል። ከዚያ በታች ያሉ ምእመናን ካሉ ግን ወደሌላ አቅራብያ ሀገረ ስብከት ተደርበው ሊገለገሉ ይገባል ማለት ነው።

፮፮. ዘወትር ገበጣ የሚጫወት ካህን ጨዋታውን ካልተወ ከሹመቱ ይሻር። ሕዝባውያንም እንዲህ ካደረጉ ከምእመናን ይለዩ። ገበጣ ማለት መሬት ተቆፍሮ በጠጠር የሚጫወቱት ነው?

መልስ፦ አዎ።

፮፯. ዐፃዌ ኖኅት ማለት ምን ማለት ነው? በቤተ ክርስትያን ድርሻውስ ምንድን ነው?

መልስ፦ ዐፃዌ ኖኅት ማለት በር ዘጊ ማለት ነው። በቤተክርስቲያን በወንዶች በር ቆሞ ወደ ቤተክርስቲያን የሚገባውን የሚቆጣጠር ነው። አሁን አሁን ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም።

፮፰. በተፈጠርክ ጊዜ እግዚአብሔር በሰጠህ መልክህ ላይ መልክ አትጨምር ማለት አትከተብ አትጠቄር። ረቂቅ ልብስ አትልበስ። ረቂቅ ልብስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ረቂቅ ልብስ ማለት አካልን የሚያሳይ ስስ ልብስ አትልበስ ማለት ነው።

፮፱. ሴት መንገድ በምትሔድበት ጊዜ በሰርመዴዋ ትከናነብ። ሰርመዴ ምንድን ነው? ሴት ዘወትር ራሷን ትከናነብ። ይህስ ዘወትር ጸጉራችንን መሸፈን አለብን ማለት ነው?

መልስ፦ ሰርመዴ የሚባለው ሴቶች ከአንገታቸው በላይ ሸፈንፈን የሚሉባት እንደ ሻርፕ ያለች ናት። ሴት በሻርፕ መከናነብ ይገባታል ማለት ነው። አዎ ሴት ልጅ ሁልጊዜም ነው ጸጉሯን መሸፋፈን ያለባት።

፸. ፍት.ነገ.፱፧፲፱፸፱ ላይ "በቁሱ ትእዛዝ አንዲት ሳትቀር አርባ ጊዜ ይግረፏቸው" ይላል። በሐዲስ ኪዳን ቀኖና ግርፋት አለ እንዴ?

መልስ፦ አዎ ግርፋት የተፈቀደባቸው ጥቂት ቀኖናዎች አሉ።

፸፩. ፍት.ነገ.12፧472 ነገሥታት ከቤተ መቅደስ ሆነው ከቀዳስያኑ ጋር የሚቆሙት ክህነት ያላቸው ናቸው ወይስ የሌላቸውም?

መልስ፦ እንደ ቅዱስ ላሊበላን ክህነትን ከንግሥና አስተባብረው ለያዙ ነገሥታት ነው ትእዛዙ። ክህነት የሌለው ንጉሥ ግን ወደ መቅደስ መግባት አይፈቀድለትም። ወደ መቅደስ የሚገባ ክህነት ያለው ነውና።

፫፪. ፍት.ነገ.12፥479 የካህናት ልብሰ ተክህኖ ቀይ እንዲሁም ሌሎች ቀለሞችን የያዙ አሉ በቅዳሴ ጊዜ የሚጠቀሟቸው። ከሥርዓቱ አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ሥርዓቱ ነጭ እንዲሆን ተናግሯል። አሁንም አንዳንድ ደብሮች እንደ ሥርዓቱ በነጭ አልባሳት ይቀድሳሉ። ስለዚህ ከነጭ ወጭ ያላቸው ደብሮችም ወደፊት ነጭ ቢያደርጓቸው መልካም ነው።

፫፫. ፍት.ነገ.13፥507 በቅዳሴ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን መባዕ ያቀረቡትን ምዕመናን ክርስትና ስም እየጠሩ መጸለይ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ነው ማለት ነው?

መልስ፦ አዎ። ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መባዐ ተብሎ በጅምላ እና የእያንዳንዳቸውን ክርስትና ስማቸውን በመጥቀስም ይጸለይላቸዋል።

፫፬. ፍት.ነገ.13፥510 ወይን ማለት ዘቢብ ማለት ነውን?

መልስ፦ አዎ። ፍሬው ደርቆ ዘቢብ ይባላል። ተጨምቆ ወደ ፈሳሽነት ሲለወጥ ደግሞ ወይን ይባላል። ካህኑ ሲጸልይበት ደግሞ በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ክርስቶስ ደምነት ተለውጦ ይቀድሰናል።

፫፭. ፍት.ነገ.14፥552 በቤት ውስጥ ከመመገባችን በፊት እና በኋላ ምን ብለን መጸለይ አለብን?

መልስ፦ ስንጀምር የምንበላውን ባርክልን ብለን አቡነ ዘበሰማያት ብለን በመስቀል አማትበን እንበላለን። ስንጨርስ ይህንን ምግብ ለሰጠን ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን። ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስን እስከ መጨረሻው ጸልየን አቡነ ዘበሰማያት ብለን መጨረስ ነው።

፫፮. ፍት.ነገ.15፥572 ላይ "በእነዚህ በታዘዙት ጾሞች ከቀኑ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ይጹሙ ከዓሣ በቀር ሥጋ አይብሉባቸው" ይላል። ዓሣ በጾም ይበላል ወይስ አይበላም?

መልስ፦ ከዓሣ በቀር የሚለው ዓሣ ሳይቀር ለማለት ነው። በጾም ወቅት ዓሣ አይበላም። ወደ አማርኛ የተረጎመው አሻሚ አድርጎት ነው እንጂ ግእዙ ዘእንበለ ዓሣ ይለዋል። ይኸውም ዓሣ ሳይቀር ማለት ነው። እንበለ የሚለው አገባብ ያለ፣ በቀር፣ ሳይቀር ተብሎ ይተረጎማልና።

፫፯. ፍት.ነገ.15፥576 ላይ "በሰባተኛው ቀን ዶሮ በጮኸ ጊዜ ከጾም ይረፉ" ይላል። ይህ ቀን መቼ ነው?

መልስ፦ ይህ ቀን ቅዳሜ ለእሑድ ባለው ሌሊት ፋሲካን (ትንሣኤን) እያከበሩ ከጾም ይረፉ ማለት ነው።

፫፯. ፍት.ነገ.15፥587 ልደት እና ጥምቀት በጾም ቀን ቢውሉ ይጾማሉ ወይስ አይጾሙም?

መልስ፦ ልደትና ጥምቀት በማንኛውም ቀን ቢውሉ በረቡዕም፣ በዓርብም ቢውሉ አይጾምም። የደስታ ቀኖች ስለሆኑ ያለ ጾም ይከበራሉ።

፫፱. ፍት.ነገ.15፥594 በጾም ወራት የሰማዕታትን በዓል ጾም ላይ ቢውልም መብል መጠጥ ተዘጋጅቶ እናከብራለን። ለምሳሌ በዓለ ቅድስት አርሴማ (ታኅሣሥ6) ስለዚህ ትክክል አይደለም ማለት ነው?

መልስ፦ በጾመ ሰዓት መብላት መጠጣት ፈጽሞ አይፈቀድም። በጾም ወቅት የሰማዕታት በዓል፣ የሌሎችም ቅዱሳን በዓላት ቢውሉ ጾመ ተጹሞ ከጾም በኋላ የጾም ምግብ መብላት፣ መጠጣት ይቻላል። ስለዚህ ታኅሣሥ 6 የፍስክ ምግብ ማዘጋጀት አይገባም። የጾም ምግብ ካዘጋጃችሁ ደግሞ ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ በመጠኑ መብላት ይቻላል።

፵. ክህነት የሌለው አያስተምር የሚለው አሁን ላይ በተለያየ ሁኔታ በሰንበት ትምህርት ቤት በግቢ ጉባኤ ተተኪ መምህራን ሰልጥነው ክህነት ሳይኖራቸው የሚያስተምሩ አሉ ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ የሐዋርያት ሲኖዶስን ስንማማር ምእመንም የተማረ ከሆነ ማስተማር ይችላል ተብሏል። ከዚህ አያስተምር መባሉ አስተምሮ አያጥምቅ ለማለት ነው። ይኸውም ዲያቆናት አያስተምሩ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

፵፩. ፍት.ነገ 12፥485 ላይ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ ወንጌሉን ማንበብ ይቻላል ማለት ነው?

መልስ፦ በሀገራችን ወንጌል በቂስ እንዲነበብ ሥርዓት ተሠርቷል። ስለዚህ በሀገራችን በሥርዓታችን እንቀጥላለን። በሌሎች ግን ዲያቆንም ወንጌልን ማንበብ እንደሚችል ሥርዓት አላቸው።

፵፪. በዐቢይ ጾም ጥምቀተ ክርስትና አይፈጸም ይላል። ከአርባና ከሰማንያ ቀን ማሳለፍ ይገባልን ወይስ ሰሞነ ሕማማት ላይ ለማለት ነው?

መልስ፦ አዎ በዐቢይ ጾም ጥምቀተ ክርስትና፣ ክህነትና የመሳሰሉት እንዳይፈጸሙ ሥርዓት ተሠርቷል። በዚህ ጊዜ ሰማንያም አርባም ቢያልፍ በሥርዓቱ ምክንያት ስለሆነ ምንም ችግር የለውም። ነገር ግን ይሞታል ብለው የሚፈሩት ሰው ካለ በዐቢይ ጾምም ቢሆን እንዲያጠምቁት የሚል ሥርዓት አለ። በሰሙነ ሕማማት ግን ጥምቀተ ክርስትና ፈጽሞ የለም።

፵፫. ቅዱስ ቁርባን ጋር ተያይዞ ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ "ሌላ ሀሳብ ያለበት አይቅረብ" ሲል ሌላ ሐሳብ ምንድን ነው? ንጹሕ ያልሆነ አይቅረብ ሲል እንደዚህ ከሆነማ መቼ ንጹሕ ሆነን ልንቀርብ ነው?

መልስ፦ ሌላ ሐሳብ ያለበት አይቁረብ ማለት ክፉ ሐሳብ ያለበት አይቁረብ ማለት ነው። ንጹሕ ያልሆነ አይቅረብ ማለት ማንኛውም ሰው ንስሓ ሳይገባ ከነኃጢአቱ በድፍረት አይቁረብ ማለት ነው። ንጹሕ ሆኖ መቁረብ ማለት ንስሓ ገብቶ መቁረብ ማለት ነው።

፹፬. ፍት.ነገ 12፥491 ላይ የማትቆርቡ ውጡ ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ በዚህ አገባብ የማትቆርቡ የተባሉ ንዑሰ ክርስቲያኖች ናቸው።

፹፭. የጉልበት ሥራ ያለበት (ገበሬ)፣ ዘጠኝ ሰዓት በሥራ ምክንያት ለመመገብ የማይችል የመንግሥት ሠራተኛ እንዴት ይጹም?

መልስ፦ ገበሬ መነኰሳት በቀን ሁለት ጊዜ ይብሉ ይኸውም ቀን ስድስት ሰዓትና በሠርክ ይላል። ሌሎቹ መነኰሳት በቀን አንድ ጊዜ ይብሉ ይኸውም በዘጠኝ ሰዓት ወይም በሠርክ ተብሏል። እንዲህ የተባለው ጾም ባልሆነ ወቅት ነው። በጾም ጊዜማ ገበሬውም፣ ቀዳሹም ሁሉም በተቀመጠው የጾም ቀኖና መሠረት ነው መጾም ያለበት። ይህ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኛውንም ሌላውንም ይመለከታል።

፹፮. አንድ ሰው ለእግዚአብሔር አሥራት በኵራት ቀዳምያት ደመዎዙ (ሀብቱ) ጥቂት ሆኖ እንዴት ማውጣት ይችላል? አሥራት አለማውጣት (አልፎ አልፎ ማውጣት) ቀኖና ያሰጣል?

መልስ፦ ያው ያለውንም የሰጠው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ከሰጠው ላይ ደግሞ ከዐሥር አንድ፣ ከመቶ ዐሥር፣ ከአንድ ሺ መቶ፣ ከአሥር ሺ አንድ ሺ መስጠት ይገባዋል። የደመዎዙን ⅒ መስጠት አለበት። አዎ አሥራን እንድንሰጥ ታዝዘን ሳለ ባለመታዘዛችን ንስሓ ልንገባና ቀኖና ልንቀበልበት ይገባናል። ሌላውን ጉዳይ ግን ከዘመኑና ከሁኔታው ጋር መወሰን የሲኖዶስ ድርሻ ነው።

፹፯. ንስሐ ሳይገቡ ቅዱስ ቁርባን ሳይቀበሉ፣ ምጽዋት ብቻዋን ታድናለች?

መልስ፦ በመንፈሳዊ ተግባራት አንዱ ብቻውን ያጸድቃል አንልም። ዐሥር በር ካለው በር ዘጠኙን ከፍተን አንዱን ብንተወው ቤታችንን ከመዘረፍ አናድነውም። ምጽዋት የራሱ የሆነ ጥቅም አለው። ቅዱስ ቁርባንን ሳይቀበሉ፣ ንስሓ ሳይገቡ ምጽዋት ብቻውን ግን አያድንም።

፹፰. የአሥራትን ገንዘብ ከምንኖርበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውጪ፣ ለነዳያን ለአብነት ተማሪዎች ለተቸገሩ ሰዎች፣ ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት፣ ለመንፈሳዊ ማኅበራት መስጠት ይቻላል?

መልስ፦ ከአጥቢያችን ውጭ ላሉ ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት መስጠት ይቻላል። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን አንዲት ናትና። ከቤተክርስቲያን ውጭ አሥራትን ለነዳያን፣ ለተቸገሩ ሰዎች፣ ለማኅበራትና ለሌሎች መስጠት ግን አይፈቀድም። አንዳንዶች ማሕበረ

ቅዱሳንን ዐሥራት የሚቀበል ብለው ይከሡታል። ነገር ግን ማሕበረ ቅዱሳን ከአባላቱ የሚቀበለው 2% ከዐሥራት ውጭ ያለና አባላቱ በፈቃዳቸው የሚሰጡት ነው።

፴፱. ፍት.ነገ.16፥625 ላይ "ለሰማዕታት ገንዘቡን የሚሰጥ ሰው እጅግ ፍጹም ይሆናል" ይላል። ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ሰማዕታት የሚላቸው ስለክርስቶስ፣ ስለእውነት መከራን የሚቀበሉ ናቸው። ስለዚህ መከራን እየተቀበሉ ላሉ ክርስቲያኖች ገንዘብ እያወጣጣን መስጠት ይገባናል ማለት ነው።

፵. ብርንዶ ክልክል ነው የተባለው ጥሬ ሥጋ ከሆነ ሰው የሚወደውና በአብዛኛው የሚጠቀመው ነውና እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ጥሬ ሥጋ በውስጡ ደም ስላለበት ሳይጠበስ እንዳይበላ ሊቃውንት በትርጓሜ ገልጸዋል። ደም አትብሉ አንድም ብርንዶውን አትብሉ የሚለው ይህንን ነው። ብርንዶ ያለው ጥሬ ሥጋን ነው።

፵፩. የወንድ ልብስና የሴት ልብስ የሚለው ምን ምን ነው? ሴት የወንድን ወንድ የሴትን ልብስ አይልበስ ይላልና።

መልስ፦ የወንድና የሴት ልብስ የሚለው ከሀገር ሀገር፣ ከዘመን ዘመን፣ ከባህል ባህል የተለያየ ነው። ስለዚህ በየሀገሩ ባህል የሴት የሚባለውን ልብስ ወንዶች፣ የወንድ የተባለውን ልብስ ሴቶች እንዳይለብሱ ተከልክሏል። የልብሱ ዓይነትና ስያሜ በዘመን፣ በባህል፣ በሀገር ልዩ ልዩ ስለሆነ አልገለጸውም።

፵፪. የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ንጹሕ ነው ይላል። ታዲያ ለምን በኦሪት ተከለከሉ?

መልስ፦ ዕፀ በለስም ንጹሕ ፍጥረት ነበር። መከልከሉ የገዢና የተገዢ ምልክት ይሆን ዘንድ ነው። በተፈጥሮ ሁሉም እንስሳት ሁሉም ፍጥረታት ንጹሓን ናቸው። በብሉይ ኪዳን እንድንበላቸውና እንዳንበላቸው የተለዩት ለእግዚአብሔር ታዛዥነታችንን እንድንገልጥባቸው ነበር። ልክ ግዝረት ለእግዚአብሔር የመታመናችን ምልክት እንደነበረው ያለ ነው።

፵፫. ሴቶች የሚያስመካ ልብስ አይልበሱ ይላል። የሚያስመካ ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የሚያስመካ ማለት ከሁሉ በላይ በልጦ ለመታየት ብለው ልብስ አይልበሱ ማለት ነው። ልብስ ዕርቃንን ለመሸፈን፣ ከብርድና ከተለያዩ ተፈጥሯዊ ነገሮች ሰውነትን ለመከላከል ያገለግላል። ከዚህ በዘለለ የእኔ ልብስ ከሁሉ ይበልጣል ተብሎ ለመመካት የሚለበስ ልብስ የሚያስመካ ልብስ ተብሏል።

፶፬. ሰዎች ካረፉ በኋላ የሚጸለየው ጸሎት ጥቅሙ ምንድን ነው?

መልስ፦ ማንኛውም ጸሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ ረድኤትን ስለሚያስገኝ የራሱ የሆነ ጥቅም አለው። ሕያዋን ለሙታን የሚያቀርቡት ጸሎትም የራሱ ጥቅም አለው። ለሟቹ በሲኦል ካለ መከራው እንዲቀልለት፣ በገነት ካለ በክብር ላይ ክብር እንዲጨመርለት ይረዳዋል።

፶፭. በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛው ቀን፣ በዘጠነኛው ቀን፣ በዐሥራ ሁለተኛው ቀን፣ በሠላሳ ቀን፣ በዐሥራ አራተኛው ቀን በስልሳኛው ቀን፣ በሰማንያ ቀን፣ በግማሽ ዓመት፣ በዓመት ተዝካር መደረጉ ምሥጢሩ ምንድን ነው?

መልስ፦ በሦስተኛው ቀን ጌታ ስለተነሣበት ነው። በሰባተኛው ቀን የሰባቱን ልዑካን ሥርዓት ሳይጠብቅ ከሞተ ይቅር በለው ተብሎ ነው። በዘጠኝ የሚደረገው በሦስት ከታጎለ ነው። በ12 የሚደረገው 12ቱ ሐዋርያት ባስተማሩት ትምህርት ሳይጸና ከሞተ ይቅር በለው ብለን ነው። በ14 የምናደርገው በሰባት ከታጎለ ነው። በሠላሳ መጋቤ አውራኑ ከዋክብትን ሳያውቅ ቢሞት ዕዳ አታድርግበት ስንል ነው። በአርባ ቀን የምናደርገው በአርባ ቀን ያገኘውን ልጅነት አሳድፎ ከሆነ ይቅር በለው ብለን ነው። በሰማንያ በአርባ ከታጎለ ነው። ለሴት ከሆነ በሰማንያ ቀኗ ያገኘችዉን ልጅነት አሳድፋ ከሆነ ይቅር በላት ብለን ነው። በግማሽ ዓመት መደረጉ በዓመት ሁለት ጊዜ ሚጠተ ብርሃናት ይደረጋል ይህን ሳያውቅ ቢሞት ዕዳ አታድርግበት ለማለት ነው። በዓመት ቢሞት መደረጉ ፀሐይ ዐውደ ዓመቷን የምትጨርሰው በዓመት አንድ ጊዜ ነው። ይህን ሳያውቅ ቢሞት ዕዳ አታድርግበት ሲል ነው። አሁን ይህንን ማወቅ ጽድቅ ይህንን አለማወቅ የሚያስጸድቅ ሆኖ አይደለም። እኒህን ላደረገ ለእግዚአብሔር ምስጋና ባያቀርብ ዕዳ ይሆንበታል ለማለት ነው።

፶፮. ዐበይት የጌታ በዓላትና ንዑሳት የጌታ በዓላት ምን ምን ናቸው? ፍት.ነገ 19፥724 የጌታ ዐበይት በዓላት 7 ናቸውን?

መልስ፦ የጌታ ዐበይት በዓላት ዘጠኝ ሲሆኑ እነዚህም፦ ዕንሰቱ፣ ልደቱ፣ ጥምቀቱ፣ ትንሣኤው፣ ሆሣዕና፣ ዕርገቱ፣ ጰራቅሊጦስ፣ ስቅለቱ (ቁጥር 740)፣ ደብረ ታቦር ናቸው። ሰባት ብሎ መናገሩ ስቅለትን ከትንሣኤ ጋር ደርቦ ቆጥሮት ነው። ጥንተ ትንሣኤው ዕለተ ዕንሰቱ በሚታሰብበት መጋቢት 29 እርሱንም አንድ ላይ ደርበው ቆጥረው ነው። ዘጠኝ ማለቱ ደግሞ የተደረቡትንም ዘርዝሮ ነው። ንዑሳት በዓላት የሚባሉት ደግሞ መስቀል (መስከረም 17 እና መጋቢት 10)፣ ስብከት፣ ብርሃን፣ ኖላዊ፣ ጌና (ታኅሣሥ 28)፣ ግዝረት (ጥር 6)፣ ልደተ ስምዖን (የካቲት 8)፣ ደብረ ዘይት እና ቃና ዘገሊላ ናቸው።

፷፮. አትብሏቸዉ ከተባሉት ምግቦች የበሽተኛን በሽታዉን የሚያርቅለት ቢሆን መብላት ይቻላል ይላልና። ካንሰር የታመመ ሰዉ ሙቶ የተገኘዉን ወይም የዉሻ ሥጋ በልተህ ትድናለህ ቢባል መብላት አለበት ነው?

መልስ፦ ሙቶ የተገኘውን እና ደምን ሰው ቢታመምም ባይታመምም ሊበላቸው የማይገቡ ኃጢአት ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው። መድኃኒት የሚሆኑት ከሆነ መብላት ይችላል ተብሎ የተነገረው ኃጢአት ያልሆኑ ነገር ግን ሥጋን ይጎዳሉ የተባሉ ከዕፀዋት፣ ከእንስሳት፣ ከአዕዋፋት የሚገኙ ምግቦች ናቸው።

፷፯. አንቀጽ 23 "ከላይ ለጣዖት የተሠዋውን መብላት አይገባም ይላል። ዝቅ ብሎ ደግሞ አምነው ቢበሉት ለጣዖት የተሠዋውንም ምንም ችግር አይፈጥርም" ይላል። ሐዋርያት በመጀመሪያው ሲኖዶስ ከልክለዋል አንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮ.10፡21 የጌታንና የአጋንንትን ጽዋዕ ልትጠጡ አትችሉም ይላል። ስለዚህ አይጋጭም?

መልስ፦ አይጋጭም። ለሌላው መሰናክል እንዳንሆን ለጣዖት የታረደውን አትብሉ ተብሏል። ነገር ግን ለሌላው መሰናክል የማንሆንበት አጋጣሚ ካለ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብለን ባርከን ብንበላው ኃጢአት አይሆንብንም። ለጣዖት ገንዘብ የለውምና።

፷፰. ፍት.ነገ.19፡740 የሐዋርያት በዓል የተባለው የትኛው ቀን ነው?

መልስ፦ የሐዋርያት በዓል የተባሉት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ያረፉባቸው ዕለታት ናቸው። (መስከረም 1፣ ጥቅምት 12፣ ጥር 4፡ ሐምሌ 2፡ ሐምሌ 5፡ ሐምሌ 10.....ወዘተ) ናቸው።

፷. ፍት.ነገ.19፡722 ዕለተ ፍሥሕ የተባለች የትኛዋ ዕለት ናት? ለምንስ በዚህ ቀን ሥጋውን ደሙን መቀበል ተከለከለ?

መልስ፦ ዕለተ ፍሥሕ የተባለች ቀዳም ሥዑር ናት። በቀዳም ሥዑር ሥጋውን ደሙን መከልከሉም ጌታ በሥጋ በመቃብር ሆኖ ስላሳለፈባት የጸም ቀን በመሆኗ ነው።

፷፩. ፍት.ነገ.19፡713 የአይሁድን ሥራ አትሥሩ ሲል በዕለተ ቀዳሚት የአይሁድ ሥራ ምን ነበር?

መልስ፦ በዕለተ ቀዳሚት አይሁድ የራሳቸውን ወግ ጨምረው የሞተ አይቀብሩም ነበር። የታመመም አይጠይቁም ነበር። እኛ ግን ቅዳሜን ስናከብር የሞተን በመቅበር፣ የታመመን በመጠየቅ መሆን ይገባል ማለት ነው።

፷፪. በበዓላት ወቅት የምንከለከለው ከየትኞች ዓይነት ሥራዎች ነው ቢገልጡልን?

መልስ፦ ከማንኛውም ሥጋዊ ሥራ ተከልክሎ መዋል ነው። መንፈሳዊ ሥራን ደግሞ መሥራት ነው። ይኸውም ማስቀደስ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፣ የታመመን መጠየቅ፣ የተጣላን ማስታረቅና የመሳሰሉት ናቸው። ዶክተሮች ቢያክሙ ኃጢአት አይሆንባቸውም። ጌታም በዕለተ ሰንበት የታመመን ፈውሷልና።

፻፫. ካህናት የወታደር ልብስ፣ የፈላስፎችን ልብስ፣ የአናጢ ልብስ አይልበሱ። ለምሳሌ በእኛ አካባቢ ካህን ሁነው አናጺዎች አሉ እንዴት ይታያል? የመነኮሳት ልብስ ደጓሳ ልብስ ሊሆን ይገባል። ደጓሳ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የወታደር ልብስ የወታደር ነው። ካህናት ደግሞ ወታደር እንዲሆኑ አልተፈቀደም። የፈላስፎችና የአናጢዎችን ልብስ አይልበሱ መባላቸው ካህናት ሙሉ ሥራቸው መንፈሳዊ ትምህርትን ማስተማር ስለሆነ ሌላ ሥራ እንዳይሠሩ ለመግለጽ ነው። ይህ ሥርዓት ታሳቢ የሚያደርገው ሰው ሁሉ ዐሥራቱን በኩራቱን እያወጣ ለካህናት ይሰጣል። ካህናት ደግሞ ሌት ከቀን ያስተምራሉ። አሁን ግን ዐሥራት፣ በኩራት፣ ቀዳምያት ሁሉም ስለማያወጣ ካህናት ራሳቸውን ለማስተዳደር ሌላ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ። ስለዚህ በዘመኑ በሲኖዶስ እንደገና መተርጎም ያለበት ሥርዓት ነው። ደጓሳ ማለት ስስ ያልሆነ ወፍራም ልብስ ማለት ነው።

፻፬. ጾም ባልሆነ ወቅት ለምሳሌ በዘመነ ቅበላና በመሳሰሉት ገዳማትና አንዳንድ አድባራት ውለው ሲቀድሱ ሌሎች ደግሞ ጠዋት ይቀድሳሉ ይሄ እንዴት ነው? ቅዳሴ ለምሳሌ ጋምቤላ አንዳንድ ጊዜ ስድስት ሰዓት ያልቃል። ይህ ተገቢ ነውን?

መልስ፦ ስለቁርባን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 19 ቁጥር 731 ትርጓሜ ላይ አምስት ጊዜያትን ጠቅሷል። እነዚህም እሑድ እሑድ ጠዋት አንድ ሰዓት፣ ቅዳሜ ቅዳሜ እና በበዓለ ኀምሳ ከሰኞ እስከ ዓርብ ጠዋት ሦስት ሰዓት፣ የትንሣኤ የልደት የጥምቀት ሌሊት (ቁጥር 727)፣ የጸሎተ ኀሙስ በሠርክ፣ በሰባቱ አጽዋማት በዘጠኝ ሰዓት ይሁን ይላል። ከሰኞ እስከ ዓርብ ጠዋት 3፡00 ሰዓት ይሁን የተባለ በበዓለ ኀምሳ ብቻ ስለሆነ በሌላው እንደ ገዳማትና እንደ ሌሎች ታላላቅ አድባራት ቀን ዘጠኝ ሰዓት ነው መሆን ያለበት። የቅዳሴ ሰዓትን ከቦታው አንጻር የማሻሻል ሥልጣን ያለው ሲኖዶስ ነው። ስለዚህ ሲኖዶስ አገዘ ከሆነ በጋምቤላ 6፡00 የሚቆረበው መልካም ነው። ሲኖዶስ ሳያገዝ በራስ አመክንዮ ተነሳሽነት ከሆነ ግን ትክክል አይደለም።

፻፭. በዐቢይ ጾም ጾመ እስከ 12/11 ሁኖ ሳለ ቅዳሴ በ9 ሰዓት መወጣቱ ስለምንድን ነው? ከቅዳሴ በኋላ መጾምስ ይቻላል?

መልስ፦ የዐቢይ ጾምን በተመለከተ ፍትሐ ነገሥት ሁለት እይታ አለው። እንደ ሀገራችን ከሰኞ እስከ ዓርብም ቅዳሴ ስላለ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ይጾማል። ሥርዓቱ እስከ 12፡00 ሰዓት፣ እስከ 11፡00 ሰዓት፣ እስከ ምሽቱ 1፡00 የሚለው የተሠራው ግን ከሰኞ እስከ

ዓርብ ቅዳሴ እንዳይኖርና በዚህ መካከል የቅዱሳን በዓላት ቢመጡ እንኳ ከረቡዕ በኋላ ከሆነ ወደፊት ባለው ቅዳሜና እሑድ፣ ከረቡዕ በፊት ከሆነ ወደ ኋላ ባለው ቅዳሜ ወይም እሑድ፣ ረቡዕ ከዋለ በስምምነት እንዲከበር ነበር። ያስቀደሰ የቆረበ ሰው ከቆረበ በኋላ መጾም አይገባውም። ያልቆረበ ካለ ግን እስከተባለው ሰዓት ቢጾም ዋጋው ይጨምርለታል።

፱፯. ፍት.ነገ.19፥715 በእሑድና በበዓላት ቀን መስገድ አይገባም። ይህ ያልተወገዘ አንቀጽ ነው ይላል። ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በዐበይት በዓላት መስገድ አይገባም። ነገር ግን ይህ አንቀጽ ውግዘት የለበትም ማለት ለምሳሌ ባሕታዊ የፍትወት ጾር ቢነሣበት በስግደት ማጥፋት ይችላል ማለት ነው።

፱፰. ፍት.ነገ.19፥734 የችንካሮችን ምልክትና የጎኑን መወጋት ምልክት አሳይቶ ለእኔ ለቶማስ አስረድቶኛልና ይላል። ይህን የሥርዓት መጽሐፍ የጻፈው ሐዋርያው ቶማስ ነው እንዴ?

መልስ፦ ይህን መጽሐፍ ከሐዋርያት ሲኖዶስ፣ በብዛት ከ318ቱ የኒቅያ ሊቃውንት፣ ከሌሎችም ሲኖዶሶች ለምሳሌ ከዕንቁራ፣ ከአንጾኪያ፣ ከስርድቅያና ከመሳሰሉት አሰባስቦ የጻፈው አብርሃም ቀሲስ ይባላል። ከሐዋርያት ሲያመጣ ሐዋርያት ቀጥታ የተናገሩትን ስለጻፈው እኔ ቶማስ አለ እንጂ ፍትሐ ነገሥትን ቶማስ የጻፈው ሆኖ አይደለም።

፱፱. ፍትሐ ነገሥት ሙሉ በሙሉ በውጭ አባቶች የተጻፈ ነው ወይስ የእኛም አባቶች ጽሑፍ ተጨምሮበታል?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት ብዙ ቅዱሳን ሊቃውንት ከጻፉት የተወጣጣ መጽሐፍ ነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም የጻፉት አልፎ አልፎ ይገኛል። ይኸውም ወበኀቤነሰ እየተባለ የተገለጸው ሥርዓት ነው። ለምሳሌ ጋብቻ በሐዋርያት ሲኖዶስ የሚከለከለው እስከ አራት ትውልድ ነው። በሀገራችን ግን እስከ ስድስት ተከልክሎ በሰባተኛው መጋባት ነው እያሉ የሠሩት የሀገራችን ሊቃውንት ናቸው።

፪፬. ፍት.ነገ.23 አትብሏቸው ከተባሉት ምግቦች የበሽተኛን በሽታውን የሚያርቅለት ቢሆን መብላት ይችላል ይላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ደዌ ይዞት ለዚያ ደዌ መድኃኒቱ የጅብ ሥጋ ቢሆን ጅብ ሊበላ ነው ማለት ነው?

መልስ፦ በሐዲስ ኪዳን ብንበላቸው ኃጢአት ይሆኑብናል የተባሉ ደምና ሞቶ ያደረን ደማዊ ፍጥረት ሥጋ ነው። ከዚህ ውጭ ያለውን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ለአካላችን ተስማሚ ያልሆኑ ነገር ግን ኃጢአት ያልሆኑ ብሎ ከዕፀዋትም፣ ከእንስሳትም፣ ከአራዊትም ጠቅሷል። ቅዱሳን ሊቃውንት ለሥጋችንም ያስባሉና ሥጋችንን የሚጎዱትንም እንዳንበላቸው መክረውናል። ሲመክሩን ግን ኃጢአት ነው ብለው

አይደለም። እንደዚህ ኃጢአት ሳይሆኑ ሰውነታችንን ግን ሊጎዱ ከሚችሉ ፍጥረታት የታመመ የሚድንባቸው ከሆነ መብላት ይችላል ብለዋል። አስተውል እነዚህ ለሌላውም የተከለከሉ ኃጢአት ናቸው ተብለው ሳይሆን ሥጋን ይጎዳሉ ተብለው ነው።

ያ፲. ሰኞ የሥራ ቀን ቢሆን እሑድ ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ ሥራ መሥራት ይቻላል?

መልስ፦ አዎ ይቻላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ሰኞ የሚባለው እኛ ከለመድነው ከእሑድ ሠርክ እስከ ሰኞ ሠርክ ያለው ነው። ስለዚህ እሑድ ለሰኞ ባለው ምሽት አጨዳ ማጨድና ሌሎችንም ሥራዎች መሥራት ይቻላል።

ያ፲፩. በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የእኅቴን ባል እኅት ልጅ ማግባት እችላለሁ?

መልስ፦ አይቻልም። ይህ የጋብቻ ዝምድናን ማፍረስ ይሆናልና።

ያ፲፪. ፍትሐ ነገሥት ቁጥር 546 ላይ "ከሚስቱ ጋር ቢሆን ሁለቱም በአንድነት ይጸልዩ። ያላመነች ብትሆን ግን ተለይቶ ብቻውን ይጸልይ። በጋብቻ አንድ የሆኑ ሰዎች በጸሎት አይለያዩ" ይላል። ባለትዳሮች አንድ ላይ ነው መጸለይ ያለባቸው? ያላመነች ጋርስ አብሮ መኖር ይቻላል?

መልስ፦ ባለትዳሮች አንድ ላይ መጸለይ ይገባቸዋል። መጀመሪያ ሌላ እምነት ኖሯቸው በኋላ ባል ወይም ሚስት ብታምንና ሌላኛው ባያምን ያመነው ብቻውን ይጸልይ ተብሏል። ካላመነች ሴት ጋር ምናልባት በፍቅር ተስባ ልታምን ስለምትችል እስከተወሰነ ጊዜ መቆየት ይቻላል። ባለማመኗ ከጸናች ግን መፋታት ነው። ይህ መጀመሪያውንም በሌላ እምነት ለነበሩ ባልና ሚስት የተነገረ ነው። እንጂ የሚያምን የማታምንን እንዲያገባ አይፈቀድለትም።

ያ፲፫. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በቤተሰብ ተጫጩ። መጀመሪያ ግን ድንግልና ይኑር አይኑር አልተነጋገሩም። ከዚያ ሁለቱ እጮኛሞች እየተነጋገሩ ሳለ አንዱ ድንግልና የሌለው ከሆነ ድንግልና የሌለው ሰው መተው ቢፈልግ ምን ማድረግ አለበት? በእጮኝነት ጊዜ የወንድየው አባት ለሴቷ የሰጠው ነገር አለ። ከዛ መተው ቢፈልግ ምን ያድርግ? ተጫጭተው ኑረው ወንድየው ድንግልና የሌለው ወይም መተው ቢፈልግ ምን ማድርግ አለበት?

መልስ፦ በእጮኝነት ጊዜ አንዱ ከአንዱ በሐሳብ የማይግባቡ ከሆነ እጮኝነት መፍረስ ይችላል። እጮኝነቱን ያልፈለገው አካል ማጫ ሰጥቶ ከነበረ ግን ማጫው አይመለስለትም። ስለዚህ እጮኝነቱን ያፈረሰው ወንዱ ከሆነና የወንድየው አባት ለሴቷ ሰጥቷት የነበረ ስጦታ ከነበረ ያንን ስጦታ እንደወሰደች ትቀራለች እንጂ አምጪ ማለት አይገባም። ድንግልና የሌላት ሴት ብትሆን ልጁ ዲያቆን ካልሆነና ከወደዳት መጋባት ይችላሉ። ሥርዓቱ ድንግሉ በተክሊል ድንግል ያልሆነው ያለተክሊል በቁርባን ይጋባሉ።

፻፲፬. ሐዋኒ (መጋቢ) ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ሐፀነ=አሳደገ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ሐዋኒ ማለት አሳዳጊ ማለት ነው። ልጆችን የሚያሳድግ የሚያስተዳድር ሰው መጋቢ (ሐዋኒ) ይባላል።

፻፲፭. ሁለት ወንድማማቾች እኅትማማቾችን ማግባት ይችላሉ?

መልስ፦ አይችሉም። የጋብቻ ዝምድናን ማፍረስ ነውና። የጋብቻ ዝምድናን ማፍረስ አይፈቀድምና።

፻፲፮. ሁለት ባለትዳሮች ከሌላ የእየራሳቸው ልጅ ወልደው ከዚያም ትዳራቸውን ሲፈቱ ሌላ ሰው ያገባሉ። ከዚያ በኋላ እነሱ ተጋብተው ከሌላ የወለዷቸውን ልጆቻቸውን ያጋቧቸዋል። ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ አይቻልም። እንዲህ ማድረግ የጋብቻ ዝምድናን ማፍረስ ነውና።

፻፲፯. ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ባልደረባ ሆኖ የተወለደ (ለመሸኛ ያህል የሽንብራ አፍንጫ የምታህል አባለ ዘር ያለው) አያግባ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አባለ ዘሩ ትንሽ የሆነ ሰው ዋዕየ ፍትወትን የማያቀል፣ ዘር የማይተካ ስለሚሆን መጀመሪያውንም እንዳያገባ ተነግሯል። አግብቶም ከሆነና ይህ ችግር ከተገኘበት ሚስቱ ልትፈታው ሥልጣን አላት ማለት ነው።

፻፲፰. ዕቁባት ምንድን ነው? ውኑዳነ ሥርዓት ምንድን ነው?

መልስ፦ ዕቁባት የሚባለው በብሉይ ኪዳን ዘመን ከሚስት ሌላ ሌሎች ሴቶችን እንደ ሚስት አድርጎ መያዝ ነው። ይህ በሐዲስ ኪዳን ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ውኑዳነ ሥርዓት ማለት በሥርዓት ከሐዲስ ኪዳኑ ሥርዓት ያነሱ ለማለት ነው። በብሉይ የነበረው ሥርዓት ከሐዲሱ ማነሱን ለመግለጽ የተነገረ ነው።

፻፲፱. አዋላጆች ወንድ ካዋለዱ 20 ቀን ሴትን ካዋላዱ 40 ቀን ሥጋዉን ደሙን አይቀበሉ ይላል። ይህ ነገር በአሁን ሰዓት እንዴት ይታያል? ዶክተሮችስ የመቁረብ ዕድላቸዉ መቼ ነዉ?

መልስ፦ በቀድሞው ዘመን ይህ ሥርዓት ተሠርቶ ነበር። ለአሁኑ ዘመን ሥርዓቱን ማሻሻል የሲኖዶስ ፈንታ ነው። እስኪሻሻል ከአበ ነፍስ ጋር እየተየጋገሩ መፍትሔ መስጠት ነው።

፻፳. በዕለተ እሑድ፣ በዕለተ ሰንበትና በጌታ በዓላት መሸጥ መለወጥ አይገባም ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ በእነዚህ ዕለታት መንፈሳዊ ነገሮችን እንድናደርግባቸው በማሰብ ቅዱሳን ሊቃውንት በእነዚህ ዕለታት ገበያ እንዳይኖር ሥርዓት ሠርተዋል። አሁን ግን ይህ ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም። እሑድ ብቻ ነው እየተከበረ ያለ እንጂ ሌሎች እየተከበሩ አይደለም።

ፀ፳፩. ሰኞ የሥራ ቀን ቢሆን እሑድ ለሰኞ ማታ መሥራት ይቻላል ተብሏል። ዓርብ ከ12፡00 ሰዓት ጀምሮ ሥጋ መብላት ይቻላል ማለት ነው?

መልስ፦ በመሠረቱ በሥነ ፍጥረት አቆጣጠር አንድ ቀን የሚባለው ከሠርክ እስከ ሠርክ ያለው ነው። ይህም ማለት ለምሳሌ እሑድ የሚባለው ዕለት እኛ ከለመድነው ከቅዳሜ ሠርክ እስከ እሑድ ሠርክ ያለው ነው። ዓርብ ከ12፡00 ሰዓት በኋላ ወደ ቅዳሜ ነው የሚቆጠር። ሰንበትን አክብሩ ጌታ አርፎባታልና ብሎ የበዓል ሥርዓትን ሲናገር በዚህ ጊዜ ሰንበት የተባለ ከዓርብ ሠርክ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ሠርክ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ይህ የበዓላት ሥርዓት ነው። የአጽዋማት ሥርዓት ከበዓላት ሥርዓት ይለያል። የጾም ቀኖና ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ነው። ለዚህም ማስረጃችን ትንሣኤ ነው። ቀዳም ሥዑርን ጹሙ ከተባልን በኋላ በእኛ አቆጣጠር ቅዳሜ ሌሊት ለእሑድ አጥቢያ ትንሣኤ ነው ብለን ተነሥተን ሥጋ እንበላለንና ነው። ዓርብ ለቅዳሜ እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት ባለው ሥጋ መብላት ግን ጾም መሻር ነው።

ፀ፳፪. ፍት.ነገ.27፥993 የባንክ ወለድ ከክርስትና ሃይማኖት አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ የባንክ ወለድ ለግለሰብ ሰጥተነው ከምንቀበለው አራጣ የተለየ ነው። የባንክ ሲስተም ገንዘባችንን ሰጥተነው በገንዘባችን ባንኩ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ሠርቶበት አትርፎ ትርፉን ለጋራ መካፈል ነው። ይህ ደግሞ ከአራጣ ወይም ብድር የሚመደብ ሳይሆን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 34 ከተገለጸው ከሽርክና የሚመደብ ነው።

ፀ፳፫. ፍት.ነገ.31፥1051 ላይ "ሦስት ባሮች የገዛ ሰው አንዱን ነጻ ቢያወጣው ይገባዋል። የቀሩትንም ሊሸጥ ቢወድ ይገባዋል" ይላል። ባሪያ መግዛት እና መሸጥ በክርስትና ሃይማኖት እንዴት ይታያል?

መልስ፦ በክርስትና ሃይማኖት ሁሉም ሰው ነጻ ሰው ነው። ነገር ግን በማሕበራዊ ሕይወት በተለያዩ ጉዳዮች የተቸገረ ሰው ከችግሩ ለመውጣት ራሱን ለሌላው ሰው አስገዝቶ (ባሪያ ሆኖ) ሊኖር ይችላል። ሲኖር ስለሚገባው ሥርዓት ደግሞ ክርስትና ይናገራል። ገዢው ባሪያውን (አገልጋዩን) እንደልጁ አድርጎ ሊንከባከበው አገልጋዩም ገዢውን እንደ አባቱ አድርጎ ሊያከብረው ይገባል ተብሏል (ኤፌ.6፥5)።

ፀ፳፬. ፍት.ነገ. 33፥1080 ጨገራታ ምንድን ነው?

መልስ፦ ጨገራታ ማለት አንድ ሰው ወይም ሁለትና ከዚያ በላይ ሰዎች ያላቸው ዓይነታው ወይም ዋናው ገንዘባቸው ነው።

፻፳፫. ፍት.ነገ.33፥1105 ላይ "በእሑድ ቀን መገበያየት የተጠላ ነው" ይላል። አንዳንድ አካባቢ ገበያ እሑድ ቀን የሚውልበት አለ (አሕዛብ የሚበዙበት ገጠራማ ቦታ)። እንደዚህ ዓይነት ቦታ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ምን ማድረግ አለባቸው?

መልስ፦ ሥርዓት እንደ ቦታው፣ እንደ ጊዜው፣ እንደባህሉ ሊሻሻል የሚችል ስለሆን እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን ለክፍሉ ሊቀ ጳጳስ አቅርቦ በሲኖዶስ እንዲታይ ማድረግ ነው። እንጂ እኛ በግላችን አሻሽለን ይህ ነው ማለት አንችልም።

፻፳፬. ፍት.ነገ. 43 ላይ ድኻ አይመስክር ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ድኻ አይመስክር የተባለበት መሠረታዊ ምክንያት በገንዘብ ምክንያት ተታልሎ ገንዘብ ላለው ሰው ሐሰተኛ ነገርን ሊመሰክር ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ምንም ድኻ ቢሆን ቆራቢና ደግነቱ የታወቀ ሰው ከሆነ ግን እንዲመሰክር ይፈቀድለታል።

፻፳፭. ፍት.ነገ.46፥1653 ሥር የሚምስ ሲባል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ሥር ማሽነት የሰይጣንን ስም እየጠሩ ሥር ቆፍረው እንፈውሳለን የሚሉ ሰዎች ናቸው። ስመ እግዚአብሔርን ጠርተን የዕፀዋትን ቅጠላቸውን፣ ሥራቸውን፣ ግንዳቸውንና ሁለመናቸውን ለእኛ ጥቅም ማዋል ግን ስር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ አያሰኝም።

፻፳፮. ፍት.ነገ.46፥1629 ላይ "እግዚአብሔርን ታመልክ ዘንድ ለእርሱም ብቻ ትሰግድ ዘንድ ተጽፏል" ይላል። እንዲሁ "ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ" ይላል (ማቴ 4፥10)። ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገዱ የተባልነው የባሕርይ ስግደትን ነው። በባሕርይው ስግደት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ማለት ነው። ከዚህ የተነገረው ስለባሕርይ ስግደት ነው። እግዚአብሔር ላከበራቸው ሰዎች የምንሰግደው ስግደት የጸጋ ስግደት ነው።

፻፳፱. ፍት.ነገ.44፥1584 ላይ "የራስ ጸጕርህን እኩሌታ አትላጭ" ይላል። የራስ ጸጕርን መቆረጥ ይገባል አይደል እንዴ?

መልስ፦ የጸጕርን እኩሌታ ተላጭቶ እኩሌታውን መተው አይገባም ማለት ነው እንጂ ፈጽሞ አትላጨ ማለት አይደለም። ወንድ ልጅ ጸጕሩን እንዳያሳድግ ሥርዓት ተሠርቷል። ሲላጭ ደግሞ ሙሉውን መላጨት እንጂ ቁንጮ፣ ጉድሮ እና የመሳሰሉትን

እያለ ከጸጉሩ የሚያስቀረው ነገር መኖር የለበትም ማለት ነው። ጺሙን ግን እንዳይላጭ ሥርዓት ተሠርቷል።

፻፴. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ንጉሥ በካህናት ላይ እንዲሁም በደጋግ ሰዎች ላይ እደ ቃሉን ለመሳደብ እደ ሥጋውን ለመማታት አያንሣ ይላል። እደ ቃሉን፣ እደ ሥጋዉን ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ እደ ሥጋዉን ማለት በሥጋ እጁ ማለት ነው። ንጉሥ ደጋግ ሰዎችን በሥጋ እጁ በጥፊ ወይም በሌላ መልኩ መማታት አይገባዉም ማለት ነው። እደ ቃል ማለት የቃል እጅ ማለት ነው። አሁን የአንደበታችን ወይም የቃላችን እጅ ኖሮት አይደለም። የአንደበታችንን ቃል ከእጅ ቆጦሮት ነው። ፍሬ ነገሩ ደጋግ ሰዎችን አትሳደብ ማለት ነው።

፻፴፩. ፍት.ነገ.43 ኢአማኒ በአማኒ መመስከር አይገባውም ይላል። ስለዚህ የፍርድ ሂደቱ ኢአማንያንን የግድ የሚያሳትፍ ሲሆንስ ምን ይደረጋል?

መልስ፦ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ ኢአማኒ በአማኒ ላይ ሊመሰክር አይገባውም። በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ግን የጋራ ሕገ መንግሥት ስላለን በዚያ መሠረት ሕገ መንግሥቱ በሚያዝዘውና በሚፈቅደው መልኩ እንዳኛለን።

፻፴፪. ፍት.ነገ. 47፥1661 ላይ "ፀሐይ ብትወጣበት ግን ለገዳዩ ሞት ይገባዋል" ሲል እንዴት ይተረጎማል?

መልስ፦ በፀሐይ በአደባባይ ሲሰርቅ የተያዘን ሌባ ወደ ዳኛ አቅርቦ ማስፈረድ እንጂ መግደል አይገባም። በአደባባይ የገደለ ሰው ካለ ግን ዳኛ በእርሱም የሞት ፍርድ ሊፈርድበት ይችላል። ይህ በሥጋዊ ፍርድ የሚተረጎም ነው እንጂ በመንፈሳዊ ሕግ ግድያ አይፈቀድም።

፻፴፫. ፍት.ነገ.48፥1719 ላይ "አፍንጫቸውንም ይፎንኑ" ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አፍንጫ መፎነን ማለት ከጫፉ ላይ መቁረጥ ማለት ነው። ይህም የተገገርነት ምልክት ነው።

፻፴፬. ፍት.ነገ.48፥1742 ያላገባ ቄስ መሆን ይችላል? ቄስ ከማግባቱ በፊት ቢሰሰን በንስሓ ዳግመኛ ወደ ክህነት ሥራ (አገልግሎት) ይመለሳል ይላል። እንዴት ይታያል? ዲያቆንስ ከማግባቱ በፊት ቢሰሰን በንስሓ ወደ አገልግሎት ይመለሳል ሲል እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ያላገባ ቄስ ሲሆን የመነኰሴ ቄስ ይሆናል። ቄስ ወይም ዲያቆን ከሰሰኑ ንስሓ ገብተው ክህነታቸው ይመለስ የሚለው ግን ሥርዋጽ ነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንት

ከራሳቸው ጳጳሳትን አይሹሙ እንደሚለው ያለ ሥርዋጽ ነው። ስለዚህ አሁን በሥርዓተ ቤተክርስቲያን አይተገበርም።

፱፬፫. ፍት.ነገ.51፥1806 መገዘር በሐዲስ ኪዳን ለክርስቲያን ግዴታ አይደለም ማለት ነው?

መልስ፦ አዎ በሐዲስ ኪዳን ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው መገዘርም አለመገዘርም አይጠቅምም። ይህ ከሃይማኖት ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም።

፱፬፬. ፍት.ነገ.51፥1809 አንድ ሰው (ሕፃን) ከመጠመቁ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ በሕመም) ሳይገዘር ቀርቶ ከተጠመቀ በኋላ ዕድሜው ከፍ ሲል መገረዝ ይችላል?

መልስ፦ ግዝረት በሐዲስ ኪዳን ከእምነት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ስለዚህ ከተጠመቀ በኋላ መገዘሩ ለጤናው ወይም ለሌላ ነገር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሊገዘር ይችላል።

፱፬፭. በሰካራም የሚፈረደው ፍርድ አእምሮ በሌለው ሰው እንደሚፈረደው ፍርድ ይሁን ሲል ይህ ሐሳብ ይብራራልኝ?

መልስ፦ ሰው ሲሰክር አእምሮውን አያውቀውም። ስካርን ዮሐንስ አፈወርቅ ሰው በፈቃዱ የሚያብደው ዕብደት ይለዋል። ስለዚህ ያበደ ሰው በሚዳኝበት ዳኝነት ይዳኛል ማለት ነው። ይህ ነገር ተደጋጋሚ ሆኖ ተመክሮ ካልተመለሰ ግን ጤነኞች በሚዳኙበት ይዳኛል።

፱፬፮. እናት አባቱን የሚበድል ልጅ ቢኖር ከእናት ከአባቱ ርስት ይነቀል ይላል። ከዚህ በኃላ ቢጸጸት በንስሐ መታጠብ አንችልም ሆይ?

መልስ፦ ተጸጽቶ እናት አባቱን በሥርዓትና በፍቅር ካገለገለ በኋላ ከርስት ገብቶ ይቆጠራል። ርስትም ይካፈላል።

፱፬፱. ባልተማረ ግብረ ገብ ባልሆነ ቄስ ከመናዘዝ መናዘዙን መተው ይሻላል። ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት ቄስ የተማረ መሆን እንዳለበት ገልጿል። ስለዚህ የተማረውን ቄስ ንስሓ አባት ማድረግ ይገባል። የማያውቅ ቄስ ላይ መናዘዝ ግን ሕክምና ከማይችል ሐኪም እንደመታከም ነው። ስለዚህ ከእንደዚህ ዓይነቱ ቄስ መናዘዙን ትቶ ከደግና የተማረ ቄስ መናዘዝ ይገባዋል ማለት ነው። ሌላ ካልተገኘ ግን ከሚሰበር ይሰንጠር ነውና ካለው መናዘዝ ይገባል እንጂ ከነኃጢአት መሞት አይገባም።